የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

# ፋሽስታዊ ግድያ በአዲግራት ዩንቨርሲቲ

ህወሃት/ወያኔ ከፅንሱ ጀምሮ ኢትዮጵያን በመከፋፈል ህዝቦቿን እርስ በእርስ እንዲጠላሉ ብሎም እንዲገዳደሉ ነበር እቅዱንም ላለፉት 26 አመታት በተግባር ላይ አውሎታል:: በዚህ ወቅት ደሞ ይባስ ብሎ በአዲግራት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ለትምህርት የሄዱትን የአማራ እና የኦሮሞ ህዝብ ተወላጆች ናቸውየተባሉትን ወጣትተማሪዎች ገድለዋቸዋል:: ብዙዋችን ደግሞ ደብድበው አቁስለዋል:: ይህ ድርጊት ሁን ተብሎ ከውስጥም ከውጭም ተጠንቶ በትግራይ ተወላጆች እንዲፈፀም የተቀነባበረ ድርጊት መሆኑን አውቀናል:: የአማራና ኦሮሞ ተወላጆች ወደ ተቋሙ ሲላኩ የወደፊቱ ሃገር መሪዎችና ባለስልጣኖች ይሆናሉ ተብለው እራሳቸውን በትምህርት እንዲያዳብሩ ነው እንጂ በመጥፎ የዘረኝነት መንፈስ ባላቸው አረመኔዎች በመኻታ ክፍላቸው ውስጥ እንዲገደሉ ወይም እንዲደበደቡ አይደለም:: የኢትዩጵያ ህዝብ ሆይ! ልጆቻችን የሚገቡበት አጥተው የድረሱልኝ ጥሪ እያሰሙ ነው:: ዛሬ የጎጃም ተወላጅ ተማሪ ሀብታሙ ያለው እና 2 ጓደኞቹ በአዲግራት ዩኒቨርስቲውስጥ ተገለዋል:: ነገስ ተራው የማነው? ዛሬ በጎንደር ዩኒቨርስቲ ፀደ ግቢ ውስጥ የአዲግራቱን ግድያ በመቃወም ግርግር ተነስቶ ነበር በተቋሙም ውስጥ የትግራይ ተወላጆች እንዳሉ ስለሚታወቅ የአጋዚ ጦር በአስቸኳይ ደርሶ ግቢውን በቁጥጥር ስር አውሎታል በተጨማሪም ለትግራይ ተወላጆች ልዩ ጥበቃ እያደረጉ ይገኛሉ:: የዘረኝነትን አፀያፊ ገፅታ መመልከት እንድንችል ይሆን ዘንድ ይህን ፅሁፍ እንድናቀርብ ተደርጓል::

ድል ለኢትዮጲያ ህዝብ ነው!

የኢትዮጵያ ህዝብ ብሄራዊ ፓርቲ! EPNP.INFO